# የቴክኒክ እገዛና ጥናት ዋና የስራ ሂደት ነባሩ የአሰራር ሁኔታ

## 1. መግቢያ

### 1.1. የስራ ሂደቱ ቅኝት

ኤችአይቪ/ኤድስን በመከላከልና በመቆጣጠር ተግባር ዘርፈ ብዙ ምላሽ ለመስጠት የሁሉም ፈጻሚ አካላት አቅም ጠንካራና ኤችአይቪ/ኤድስንና ተጽእኖውን መመከት የሚችል መሆን እንዳለበት ይታመናል፡፡ አሁን ባለው አሰራር የሴክሬታሪያት ጽ/ቤቱ ባለሙያዎች በተለያዩ አጋጣሚዎች ካደረጉት የፈጻሚዎች አቅም ክፍተት ምልከታ ወይም የተለያዩ ረጂ ድርቶች ካቀረቡት በመረጡት ጉዳይ የአቅም ግንባታ ይካሄድ ጥያቄ መሰረት የቴክኒክ እገዛ ፕሮፖዛል በባለሙያዎች ይዘጋጃል፡፡ ፕሮፖዛሉ በገንዘብ እንደሚደገፍ ሲረጋገጥና ሲፀድቅ አቅማቸው ሊገነባላቸው ይገባል የተባሉ ፈጻሚዎች በባለሙያዎች ይጠቆሙና ጥሪ ይደረግላቸዋል፡፡

የቴክኒክ እገዛውን አሰጣጥንም በተመለከተ ወጥና ሁልጊዜ የሚጠበቅ ደረጃ ባይኖረውም በተቻለ መጠን የጥራት ደረጃውን ጠብቆ እንዲከናወን ይደረጋል፡፡ በአንዳንድ የቴክኒክ እገዛ ስራዎች ማጠቃለያ ላይ አገልግሎቱ ላይ ያላቸው አስተያየት ግብረመልስ የሚጠየቅና የሚሰበሰብ ቢሆንም ብዙውን ጊዜ ከግብረመልሱ በመነሳት የሚወሰድ እርምጃ የለም፡፡ የቴክኒክ እገዛ የሚሰጠውም በተለያዩ ክፍሎች በተበታተነ መልክ ነበር፡፡ በጥናትና ምርምር ምላሽ የሚያገኙ በርካታ ጉዳዮች ቢኖሩም ከጅምር ያለፈ ምላሽ የተሰጠባቸው የሉም፡፡ በዚሁ ሳቢያ አድቮኬሲ ሊካሄድባቸው ከሚገባ በርካታ ጉዳዮች ውስጥ ያለበቂ ጥናት በተወሰኑት ላይ ብቻ አድቮኬሲ ተካሂዷል፡፡ ባጠቃላይ በነባሩ አሰራር ለደንበኞች መሰጠት የሚገባውን ያህል የቴክኒክ እገዛ ሳይሰጥ ቆይቷል፡፡

ነባሩን አሰራር በመለወጥ የተሻለ ውጤት ለማምጣት የቴክኒክ እገዛና ጥናት ነባሩ አሰራር ያሉበትን ችግሮች ማወቅና አዲሱ አሰራር ያመጣውን ልዩነት መለየት እንዲቻል ነባሩን አሰራር በዝርዝር ማየትና ማጥናት አስፈልጓል፡፡ በዚህም መሰረት ለቴክኒክ እገዛና ጥናት የስራ ሂደት አሁን እየተሰራበት ያለው የስራ ሂደት ሁኔታ ምን እንደሚመስል በዚህ ጥናት ተዳስሶ ቀርቧል፡፡

## *1.2. የጥናቱ ዓላማ*

አሁን ያለው የቴክኒክ እገዛ አሰጣጥ ምን እንደሚመስልና ለደንበኞች እየተሰጠ ያለው አገልግሎት ደረጃን ለመቃኘት ነው፡፡

## *1.3. የጥናቱ ግብ*

ደንበኞችን የሚያረካ አዲስ የስራ ሂደት መዘርጋት

## *1.4. የጥናቱ አስፈላጊነት፡-*

ነባሩን አሰራር በመቃኘት ለአዲሱ የስራ ሂደት ጥናት መነሻ ማግኘት ነው፡፡

## *1.5. የጥናቱ ወሰን /Scope/*

- ጥናቱ የሴክሬታሪያት ጽ/ቤቱን ነባር የቴክኒክ እገዛ አሰጣጥ ይቃኛል፡፡
- ጽ/ቤቱ ካሉት የሥራ ሂደቶች መካከል የቴክኒክ እገዛና ጥናት ዋና የስራ ሂደት አሁን ያለበትን ሁኔታ ያጠናል፡፡

## *1.6. የጥናቱ ዘዴ*

- ከደንበኞች መካከል በናሙና የተመረጡ መ/ቤቶች በነባሩ የቴክኒክ እገዛ አሰጣጥ ላይ በመጠይቅ አስተያየት እንዲሰጡ ማድረግ
- ከሴክሬታሪያት ጽ/ቤቱ የስራ ክፍሎችና የዞን ማስተባበሪያ ጽ/ቤቶች በነባሩ የቴክኒክ እገዛ አሰጣጥ ላይ በመጠይቅ አስተያየት እንዲሰጡ ማድረግ
- የሴክሬታሪያት ጽ/ቤቱን የውስጥ መመሪያዎችና ደንቦችን መዳሰስ
- ለመሰረታዊ የስራ ለውጥ ሂደት ጥናት አጋዥ የሆኑ ዋቢ መጻህፍትን መቃኘትና የአሰራር መርሆዎችን መውሰድ
- የቴክኒክ እገዛ የመስጫ መመሪያዎች ማኑዋሎች አሰራሮችና ሰነዶችን መቃኘት
- ለመሰረታዊ የስራ ለውጥ ሂደት ጥናት ከተመደቡ አማካሪዎች /ቁሳሮች/ ጋር መወያየት

# 2. ነባሩን የስራ ሂደት መተንተን

## *2.1. ነበሩ የስራ ሂደት የት ጀምሮ የት ያበቃል?*

- የስራ ሂደቱ የጽ/ቤቱ ባለሙያዎች የአቅም ክፍተት ምልከታ ሲያደርጉ ወይም ለጋሾች የአቅም ግንባታ የመስጠት ፍላጎታቸውን ሲያሳውቁ ይጀምራል፡፡
- አድቮኬሲ በማካሄድ ይጠናቀቃል፡፡

## *2.2. የስራ ሂደቱ ግብዓት፣ ውጤትና የግብ ስኬት*

- ግብዓት :- ኤችአይቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችል የቴክኒክ እገዛ የማግኘትና በጥናት የተደገፈ የሥራ አቅጣጫ የመያዝ ፍላጎት

- ውጤት :- የፈጻሚዎችን የመፈፀም አቅም የሚገነባ የተጠናከረ የቴክኒክ እገዛና በጥናት የተደገፈ የፕሮግራም አፈጻጸም

- የግብ ስኬት :- በቴክኒክ እገዛ በተጠናከረ አቅምና አመራር ፈጻሚዎችና ሕብረተሰቡ ኤችአይቪ/ኤድስን እንዲከላከሉና እንዲቆጣጠሩ ማስቻል

## 2.3 የቴክኒክ እገዛና ጥናት ዋና የስራ ሂደት ፍሰት (High Level Map)



## 2.4. የነባሩ የስራ ሂደት ዝርዝር ፍሰት (Detail Map)




1
ስትራቴጅዎችንና ዝርዝር የአፈፃፀም ፕሮግራሞችን መቀበል
ስትራቴጅዎችንና ዝርዝር የአፈፃፀም ፕሮግራሞችን ክልላዊ ይዘት መስጠት
ስትራቴጅዎችንና ዝርዝር የአፈፃፀም ፕሮግራሞችን የማስተዋወቂያ ፕሮፖዛል ማዘጋጀት
የለም
ፕሮፖዛል ማስፀደቅ
አዎ
ስትራቴጅዎችንና ዝርዝር የአፈፃፀም ፕሮግራሞችን ማስተዋወቅ
ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያዎችን ማስተላለፍ
የሕዝብ ንቅናቄ በፈፃሚዎች ይተባበራል
የመመሪያ አፈፃፀም ክትትል
ጠንካራ ጎኖችን ለማበረታታት ደካማ ጎኖችን ለማስወገድ የሚያስችል ሀሳብ ማመንጨት
2


2
የታዩ ጠንካራና ደካማ ጎኖችን መለየት
የአድቮኬሲ ስልቶችን መንደፍ
የለም
የተነደፉ የአድቮኬሲ ስልቶችን ማስፀደቅ
አዎ
የሚመለከታቸውን አካላት ማሳተፍ
አድቮኬሲ ማካሄድ
በቴክኒክ እገዛ በተጠናከረ አቅምና አመራር የሕብረተሰቡ ኤችአይቪ/ኤድስን መከላከልና መቆጣጠር

# 3. ነባሩን የስራ ሂደት ማጥናት

## *3.1. የስራ ሂደቱ ምን ውጤት ያስገኛል?*

ኤች አይ ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችል ጠንካራ አቅም ያላቸው ፈፃሚ አካላትና ለስራቸው የሚያግዙ የጥናት ውጤቶች

## *3.2. የስራ ሂደቱ ይህን ውጤት ለምን አስገኘ?*

የኤች አይ ቪ/ኤድስን ወረርሽኝ ለመከላከልና ለመቆጣጠር በዘርፈ ጠንካራ የአመራርና የመፈፀም አቅም ያላቸው ፈፃሚዎች ስለሚያስፈልጉ

## *3.3. የስራ ሂደቱ ደንበኞችና ፍላጎት*

| ተ.ቁ | ደንበኞች | የደንበኞች ፍላጐት |
|---|---|---|
| 1. | የመንግስት መ/ቤቶች | - የሚፈልጉትን አይነት የቴክኒክ እገዛ ማግኘት<br>- ከሌሎች አካላት ጋር በጋራ መስራት በሚፈለጉባቸው ጉዳዮች መቀናጀት<br>- ለስራቸው የሚያግዙ የጥናት ውጤቶች |
| 2. | መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች | |
| 3. | የእምነት ተቋማት | |
| 4. | ማህበራትና ማህበረሰብ አቀፍ ተቋማት | |
| 5. | ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት | |
| 6. | ከፍተኛ የልማት ተቋማትና ኘሮጀክቶች | |
| 7. | ግለሰቦችና የግል ድርጅቶች | |

## *3.4. ሌሎች ባለድርሻዎችና ፍላጎቶቻቸው*

| ተ.ቁ | ባለድርሻዎች | ድርሻቸው | የባለድርሻዎች ፍላጎት |
|---|---|---|---|
| 1) | የቴክኒክ እገዛ የመስጠት አቅም ፍላጎት ያላቸው ድርጅቶች | በራሳቸው ገንዘብ ወይም በክፍያ የአቅም ግንባታ ስራ በጋራ ማካሄድ | የተቋቋሙበትን ዓላማ ለማሳካት ምቹ ሁኔታ ማግኘት |
| 2) | የትብብር መድረኮችን የመመስረትና የማገዝ ፍላጎት ያላቸው ድርጅቶች | ለትብብር መድረኮች የአቅም ግንባታና ድጋፍ በጋራ መስጠት | ፈፃሚዎች እንዲሰባሰቡላቸውና ለማገዝ በሚያስችል መልክ ተደራጅተው ማግኘት |
| 3) | ስራዎችን በገንዘብ ማገዝ የሚፈልጉ ረጅ ድርጅቶች | ለአቅም ግንባታ የሚውል ገንዘብን መስጠት | ገንዘባቸው ላለሙት ዓላማ ውሎ በወቅቱ ማወራረድ |
| 4) | የኤችአይቪ/ኤድስ መከ/ መቆ/ ም/ቤትና የክልሉ ም/ቤት | በክልሉ ኤችአይቪ/ኤድስን መከ/ መቆ/ የሚያስችል አቅም መገንባቱን ማረጋገጥ | በተጠናከረ አቅም ኤችአይቪ/ ኤድስን መከ/ መቆ/ መቻል |

### 3.5 የነባሩ የስራ ሂደት የአፈጻጸም ደረጃ (Performance Baseline)

| ተራ ቁ. | ዋናዋና ተግባራት | ደረጃ (Step) | ጊዜ (Time) (በቀን) | ወጪ (Cost) | ጥራት (Quality) |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የአቅም ክፍተት ደሰሳ/ምልከታ | 0 | 0 | 0 | በጣም ዝቅተኛ |
| 2 | የቴክኒክ እገዛ ዕቅድ ማዘጋጀት | 2 | 5x4=20 | 92,200 | ዝቅተኛ |
| 3 | የቴክኒክ እገዛ መስጠት | 4 | 4x4=16 | 63,040 | መካከለኛ |
| 4 | ስትራቴጅዎተንና ዝርዝር የአፈፃፀም ኘሮግራሞችን ክለሳዊ ይዘት መስጠት | 7 | 20 | 22,900 | መካከለኛ |
| 5 | ስትራቴጅዎችንና ዝርዝር የአፈፃፀም ፕሮግራመችን ማስተዋወቅ | 10 | 20 | 291,450 | መካከለኛ |
| 6 | ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያዎችን ማስተላለፍ | 11 | 5 | 15,150 | መካከለኛ |
| 7 | አድቮኬሲ ማካሄድ | 18 | 10 | 582,900 | ዝቅተኛ |
| | ድምር | 57 | 91 | 1,067,640 | |

የቴክኒክ እገዛ ሥራዎች በየሩብ ዓመቱ ስለሚተገበሩ በአራት ተባዝቶ ተቀምጧል፡፡

የመረጃው ምንጭ ከደንበኞችና ከባለሙያዎች በመጠይቅ የተሰበሰበ መረጃ ነው፡፡

## 3.6. የስራ ሂደቱ ችግሮች፣ ህጎችና ታሳቢዎች (Problems, Rules & Assumptions)

| ተ.ቁ (No) | ችግር (Problem) | የችግሩ ምንጭ (Rules) | ታሳቢዎች (Assumptions) | ታሳቢዎችን መሻር (Untrue Assumptions) |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ደንበኞች ለሚያስፈልጋቸው የቴክኒክ እገዛ ወቅታዊ ምላሽ ባለማግኘታቸው የአፈጻጸም መዘግየት ማስከተሉ | ልማዳዊው አሰራር የቴክኒክ እገዛ ደንበኞች በጠየቁ ጊዜ ሳይሆን ጽ/ቤቱ ባቀደው ጊዜ እንዲሰጥ የሚደረግ መሆኑ | የሚያስፈልገውን የቴክኒክ እገዛ የጽ/ቤቱ ባለሙያዎች ያውቁታል ብሎ ማሰብ | የባለሙያዎች ምልከታ በደንበኞች ፍላጎት ዳሰሳ ስላልታገዘ ፈጣን ምላሽ መስጠት አላስቻለም |
| 2 | ደንበኞች ደረጃውን የጠበቀና ለደረጃቸዉ የሚመጥን የቴክኒክ እገዛ ባለማግኘታቸው የአፈጻጸማቸው ጥራት ማነሱ | ልማዳዊው አሰራር ባለሙያዎች ያቀረቡትን የቴክኒክ እገዛ አይነት በቀጥታ እንዲሰጥ ማድረጉ | ብቁ ባለሙያዎች እስካሉ ድረስ ደረጃውን የጠበቀ የቴክኒክ እገዛ ይኖራል ብሎ ማሰብ | ያለ ግልጽ ደረጃ የሚከናወኑ የቴክኒክ እገዛዎች ደረጃቸውን አልጠበቁም |
| 3 | ደንበኞች ቀጣይነት ያለው የቴክኒክ እገዛ ባለማግኘታቸው ፕሮግራሞቻቸው በበቂ መጠንና ጥራት መፈጸም አለመቻላቸው | አንድ ጊዜ የተሰጠ የቴክኒክ እገዛ እንደ በቂ አድርጎ የመውሰድ ልማዳዊ አሰራር መኖሩ | ደንበኞች አንድ ጊዜ አቅጣጫ የሚያስይዝ የቴክኒክ እገዛ ካገኙ በራሳቸው ጥረት ክፍተቶቻቸውን በመሙላት ውጤታማ ስራ ይሰራሉ ብሎ ማሰብ | ያለተከታታይ የቴክኒክ እገዛ በአንድ ጊዜ በተያዘ አቅጣጫ ብቻ ደንበኞች ውጤታማ ስራ መስራት አልቻሉም፡፡ |
| 4 | የትብብር መድረኮች ባለመጠናከራቸው በደንበኞች ላይ የሀብት ብክነት መከሰቱና አድሆኬሲ ማካሄድ አለመቻላቸው | • በልማዳዊ አሰራር የማስተባበሪያ ዋና ስልት የትብብር መድረኮችን ሳይሆን ጽ/ቤቱ እራሱን ማድረጉ<br>• የትብብር መድረኮች ሕጋዊ እውቅና እንዲያገኙ የማያደርግ አሰራር መኖሩ | • ፈጻሚዎች በትብብር መድረክ ባይደራጁም በተናጠል ማስተባበር ይቻላል ብሎ ማሰብ<br>• የትብብር መድረኮች አባላቶች በተናጠል ሕጋዊ እውቅና ስላላቸው ተደራቢ እውቅና አያስፈልግም ብሎ ማሰብ | • ያለ ትብብር መድረኮች ደንበኞችን በተናጠል በማስተባበር ተፈላጊው ውጤት አልተገኘም<br>• የሕጋዊ እውቅና ማጣት ከተለያዩ አካላት ጋር ግንኙነት ከማድረግ ማገድና በአባል ድርጅቶቹ ተአማኒነትን ማሳጣት አመጣ እንጂ በተናጠል እውቅና ውጤት አልመጣም |

| ተ.ቁ (No) | ችግር (Problem) | የችግሩ ምንጭ (Rules) | ታሳቢዎች (Assumptions) | ታሳቢዎችን መሻር (Untrue Assumptions) |
|---|---|---|---|---|
| 5 | ደንበኞች በጥናትና ምርምር ውጤቶች ባለመታገዛቸው ውጤታማነታቸው ባልተረጋገጠ ፕሮግራሞች ላይ ጊዜና ገንዘባቸውን ለማዋል መገደዳቸው | ኤችአይቪ/ኤድስ የአስቸኳይ ጊዜ ስራ በመሆኑ በቀጥታ ወደ ትግበራ እንግባ የሚል ዓለም አቀፋዊና አገራዊ አቅጣጫ መኖሩ | ገንዘብን በጥናት ላይ ከማዋል ባስቸኳይ ለተለያዩ ፕሮግራሞች ቢውል ኤችአይቪ /ኤድስን ለመከ/መቆ/ ያስችላል ብሎ ማሰብ | ኤችአይቪ /ኤድስን የመከ/መቆ/ ፕሮግራሞች በጥናት ቢታገዙ የበለጠ ውጤታማና የተሻለ የሀብት አጠቃቀም ይኖራል። |

# አባሪ 1፤ የፈፃሚዎች አስተያየት ማሰባሰቢያ መጠይቅ

**የፈፃሚዎች አስተያየት ማሰባሰቢያ መጠይቅ**

**የቴክኒክ እገዛና ጥናት ዋና የስራ ሂደት**

**በተደረገላቸው የቴክኒክ እገዛ ላይ**

**የፈፃሚዎች አስተያየት ማሰባሰቢያ መጠይቅ**

የፈፃሚው መ/ቤት ዓይነት

ሀ. መንግስታዊ ለ. መያድ ሐ. ማህበር መ. ሌላ ______________

1. በቴክኒክ እገዛ

1.1. ሀ. በኤች አይ ቪ/ኤድስ አስተቃቀድ ስልጠና ወይም የቴክኒክ እገዛ አግኝተዋል?
   አዎ ________ የለም __________

   ለ. መልሰዎ አዎ ከሆነ እገዛው በቂ ነው _____ በቂ አይደለም ________

   ሐ. መልስዎ የለም ከሆነ እገዛውን ይፈልጉት ነበር? አዎ_____ የለም______

1.2. ሀ. የኤች አይ ቪን ጉዳይ ከመደበኛ ስራ ጋር አዋህዶ ለመስራት የሚያስችል (የሜይንስትሪሚንግ) ክህሎት አግኝተዋል? አዎ _____ የለም ______

   ለ. መልስዎ አዎ ከሆነ በቂ ነው ______ በቂ አይደለም _________

   ሐ. መልስዎ የለም ከሆነ ቢያገኙ አስፈላጊዎ (ጠቃሚ) ነበር ብለው ያምናሉ?
   አዎ ____ የለም _______

1.3. ሀ. የኤድስ ፈንድን አመሠራረትና አተገባበር በተመለከተ እገዛ አግኝተዋል?
   አዎ ________ የለም _________

   ለ. መልስዎ አዎ ከሆነ እገዛው በቂ ነበር _____ በቂ አልነበረም ____

   ሐ. መልስዎ የለም ከሆነ እገዛውን ማግኘት አስፈላጊዎ ነው
   አዎ _______የለም _____

1.4. ሀ. የኤድስ ፈንድ መመሪያ አለዎት አዎ _____ የለም _________

   ለ. መልስዎ አዎ ከሆነ መመሪያው ለመስራት በቂ ነው_____
   በቂ አልነበረም _____

   ሐ. መልስዎ የለም ከሆነ መመሪያው ያስፈለግዎታል? አዎ __ የለም ____

1.5. ሀ. ድጋፍና ክብካቤን በተመለከተ በቂ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችልዎ ዕውቀትና ክህሎት አግኝተዋል? አዎ ______ የለም ______

ለ. መልስዎ አዎ ከሆነ እገዛው በቂ __________በቂ አልነበረም ______

ሐ. መልስዎ የለም ከሆነ መኖሩ ጠቃሚ ነበር _____ አልነበረም __________

1.6. ሀ. የድጋፍና ክብካቤ መመሪያ አለዎት አዎ _________ የለም ______

ለ. መልስዎ አዎ ከሆነ መመሪያው ለስራ በቂ ነው _______ አይደለም ______

ሐ. መልስዎ የለም ከሆነ መመሪያው ቢኖርዎት ለስራ ያግዛል ______ አያግዝም _____

1.7. ሀ. ከሌሎች ጋር በአጋርነት (Partnership) ለመስራት የሚያስችልዎ ዕውቀት/ክህሎት አግኝተዋል? አዎ _________ የለም ______

ለ. መልስዎ አዎ ከሆነ እገዛው በቂ ነበር ______በቂ አልነበረም __________

ሐ. መልስዎ የለም ከሆነ መኖሩ ጠቃሚ ነበር _____ አልነበረም __________

1.8. ኤች አይ ቪ/ኤድስን የመከ/መቆ ስራዎች አፈፃፀምን በተዋረድ ላሉት የመ/ቤቱ አካላት ክትትል ማድረግ የሚያስችልዎት ክህሎት/ዕውቀት አግኝተዋል? አዎ ______ የለም ___________

1.9. ሀ. በኤች አይ ቪ/ኤድስ መከ/መቆ መሠረታው ዕውቀት የሚያስጨብጥ እገዛ (በስልጠና ወይም በሌላ መልክ) አግኝተዋል? አዎ _____ የለም ______

ለ. መልስዎ አዎ ከሆነ እገዛው በቂ ነው _______ በቂ አይደለም __________

ሐ. መልስዎ የለም ከሆነ መኖሩ ጠቃሚ ነበር ________ አልነበረም ________

1.10. ሀ. የማህበረሰብ ውይይት ለማካሄድ የሚያስችል እውቀት/ክህሎት አግኝተዋል? አዎ ___________ የለም ______

ለ. መልስዎ አዎ ከሆነ እገዛው በቂ ነው _____ በቂ አይደለም __________

ሐ. መልስዎ የለም ከሆነ መኖሩ ጠቃሚ ነበር ______ አልነበረም ________

1.11. ሀ. የኤች አይ ቪ/ኤድስ መከ/መቆ ስራዎች ሪፖርት አቀራረብን በተመለከተ ዕውቀት/ክህሎት አግኝተዋል አዎ __________ የለም ______

ለ. መልስዎ አዎ ከሆነ እገዛው በቂ ነው _________ በቂ አይደለም _______

ሐ. መልስዎ የለም ከሆነ መኖሩ ጠቃሚ ነበር _____ አልነበረም ________

1.12. ሀ. ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከ/መቆ ስራዎችን የመምራት (Leadership) ክህሎት/ዕውቀት አግኝተዋል? አዎ _________ የለም _________

ለ. መልስዎ አዎ ከሆነ እገዛው በቂ ነው ________ በቂ አይደለም ________

ሐ. መልስዎ የለም ከሆነ መኖሩ ጠቃሚ ነበር ______ አልነበረም ________

1.13. ሀ. የኤች አይ ቪ/ኤድስ መከ/መቆ ስራዎችን ለማካሄድ አስበው በገጠመዎት ችግር ምክንያት የቴክኒክ እገዛ ፈልገው ወደ ሴክሬታሪያት ጽ/ቤቱ መጥተው ያውቃሉ? አዎ ________ የለም ______

ለ. መልስዎ አዎ ከሆነ ያገኙት እገዛ በቂ ነበር _____ በቂ አልነበረም _____ እገዛ ሳይሰጠኝ ተመልሻለሁ ____________

ሐ. መልስዎ የለም ከሆነ ያልመጡት እገዛ ስላላስፈለገዎት ነው __________ እገዛ ማግኘት እንደሚችሉ ባለማወቅ ___________ አላገኝም ብሎ በማሰብ ___________ ሌላ ________________________

1.14. ኤች አይ ቪ/ኤድስን መከ/መቆ በተመለከተ የበለጠ መስራት እንዲችሉ ከጽ/ቤታችን ምን የቴክኒክ (የሙያ) እገዛ ይፈልጋሉ በአይነት ይዘርዝሩ

ሀ. ___________________________________________

ለ. ___________________________________________

ሐ.___________________________________________

መ. ___________________________________________

ሠ. ___________________________________________

ረ. ___________________________________________

2. የሕዝብ ንቅናቄ

2.1 መ/ቤትዎ ከሠራተኛው ጀምሮ ኤች አይ ቪ/ኤድስን ለመከ/መቆ የሕዝብ ንቅናቄ ለማድረግ ባከናወናቸው ስራዎች ያጋጠሙ ችግሮች ነበሩ?

ሀ. አዎ _________ ለ. የለም _________

2.2 ሀ. በሕዝብ ንቅናቄ አፈፃፀም ወቅት ለተፈጠሩ ችግሮች ከሴክሬታሪያት ጽ/ቤታችን የቴክኒክ እገዛ ጠይቀዋል? ሀ. አዎ ________ለ. የለም _________

ለ. መልስዎ አዎ ከሆነ ያገኙት ምላሽ ምን ይመስላል? __________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

3. ጥናትና ምርምር

3.1 ሀ. ኤች አይ ቪ/ኤድስ በሴክተሩ ወይም መ/ቤትዎ በሚያገለግለው ሕብረተሰብና በመ/ቤትዎ ሠራተኞችና ስራ ላይ ያደረሰው ተፅዕኖ ተጠንቷል?

አዎ _____________ የለም ________

ለ. መልስዎ አዎ ከሆነ ከጥናቱ በመነሳት የተወሰደው እርምጃ ይገለፅ? ______

______________________________________________________________

______________________________________________________________

ሐ. መልስዎ የለም ከሆነ ላለመጠናቱ ችግሩ ምን ነበር? __________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

3.2 ሀ. በ3.1 የተገለፀው ተመሳሳይ ጥናት ለማካሄድ መ/ቤትዎ ከጽ/ቤታችን የሚፈልገው የቴክኒክ እገዛ አለ ____________ የለም ____________

ለ. መልስዎ አለ ከሆነ ይገለፅ ________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

3.3 ሀ. ኤች አይ ቪ/ኤድስን በተመለከተ የተካሄዱ ጥናቶችን ውጤት የያዘ ሰነድ ደርሶዎት ያውቃል? አዎ __________ የለም ____________

ለ. መልስዎ አዎ ከሆነ የጥናቱ ውጤት ለስራዎ ደጋፊ ነበር? አዎ ________

የለም ________

3.4 ሀ. ከመ/ቤትዎ ጋር ተቀራራቢነት ባለው ሁኔታ መጠናት የሚገባው የኤች አይ ቪ/ኤድስን የተመለከተ ጉዳይ አለ _______ የለም ______

ለ. ካለ ቢጠቁሙን ________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

3.5 ሀ. በክልሉ ወይም በአካባቢዎ ለኤች አይ ቪ/ኤድስ መስፋፋት አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ደንቦች፣ አዋጆች፣ አሠራሮች፣ ልማዳዊ ድርጊቶች፣ እምነታዊ ድርጊቶች አሉ __________ የሉም ___________

ለ. ካሉ ቢጠቅሱልን ________________________________________________

________________________________________________________________

________________________________________________________________

ሐ. እነዚህን ችግሮች ለማቃለል ጽ/ቤታችን ምን ቢሠራ ጥሩ ይመስልዎታል? _

________________________________________________________________

________________________________________________________________

3.6 ሀ. ኤች አይ ቪ/ኤድስን በተመለከተ የሚፈልጉት ግን ያላገኙት የጥናት ውጤት አለ ______ የለም ______

ለ. ካለ ቢገልፁልን __________________________________________________

________________________________________________________________

________________________________________________________________

3.7 ኤች አይ ቪ/ኤድስ ላይ ሊካሄዱ የሚባቸውንና የተካሄዱ ጥናቶችን አስመልክቶ ጠቅላላ አስተያየት ካለዎች ___________________________________________

________________________________________________________________

________________________________________________________________

________________________________________________________________

3.8 አጠቃላይ ጽ/ቤታችን ሊያተኩርበት ይገባል የሚሏቸው ጉዳዮች ካሉ ይግለፁ __

________________________________________________________________

________________________________________________________________

________________________________________________________________

**መጠይቁን ጊዜ ወስደው ስለሞሉልን እናመሰግናለን፡፡**

# አባሪ 2፡ የጽ/ቤቱ የስራ ክፍሎች አስተያየት ማሰባሰብ መጠይቅ

**የአብክመ ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ሴ/ጽ/ቤት**

**የቴክኒክ እገዛና ጥናት ዋና የስራ ሂደት**

**ከተለያዩ የጽ/ቤቱ የስራ ክፍሎች**

**አስተያየት ማሰባሰብ መጠይቅ**

የክፍሉ ስም፡- ______________________________

1. የስራ ክፍልዎ ለደንበኞች የቴክኒክ እገዛ ለመስጠት መነሻ የሚያደርጋቸው ነገሮች አሉ? ሀ. አዎ ለ. የለም
2. ለ1ኛው ጥያቄ መልስዎ “አዎ” ከሆነ ለደንበኞች የቴክኒክ እገዛ በመስጠት የስራ ክፍልዎ ምንን መነሻ ያደርግ ነበር? ______________________________
______________________________
______________________________
______________________________
3. ለ1ኛው ጥያቄ መልስዎ “የለም” ከሆነ ለምን? ______________________________
______________________________
______________________________
______________________________
4. የስራ ክፍልዎ ከደንበኞች የቴክኒክ እገዛ ጥያቄዎች ተቀብሎ ያውቃል?
ሀ. አዎ ለ. የለም
5. ለ4ኛው ጥያቄ መልስዎ “አዎ” ከሆነ የቴክኒክ እገዛ ጥያቄዎች በወቅቱ ተገቢውን ምላሽ ለመስጠት ምን ምን ተግባራት ተከናወኑ? ______________________________
______________________________
______________________________
______________________________

6. ለ4ኛው ጥያቄ መልስዎ “የለም” ከሆነ ደንበኞች የቴክኒክ ድጋፍ እንዲያገኙ የደንበኞች የአፈፃፀም አቅም ክፍተት ዳሰሳ በስራ ክፍልዎ ተሰርቶ ያውቃል?

   ሀ. አዎ ለ. የለም

7. የስራ ክፍልዎ የቴክኒክ እገዛ ለመስጠት በዕቅድ ይንቀሳቀስ ነበር?

   ሀ. አዎ ለ. የለም

8. በስራ ክፍልዎ ይሰጡ የነበሩ የቴክኒክ እገዛዎች ዋና ዋናዎቹን ይዘርዝሩ፡-_________

   ____________________________________________________________________

   ____________________________________________________________________

   ____________________________________________________________________

   ____________________________________________________________________

9. የስራ ክፍልዎ ማድረግ የሚገባው ነገር ግን ያላደረጋቸው የቴክኒክ እገዛ ተግባራት አሉ ብለው ያምናሉ? ሀ. አዎ ለ. የለም

10. ለ9ኛው ጥያቄ መልስዎ “አዎ” ከሆነ ምን ምን ነበሩ? _________________________

   ____________________________________________________________________

   ____________________________________________________________________

   ______________________________________________________________

11. የስራ ክፍልዎ በጥናትና ምርመር አኳያ ምን ምን ተግባራት አከናውኗል? _______

   ____________________________________________________________________

   ____________________________________________________________________

   ____________________________________________________________________

12. ከደንበኞች ፍላጎት አኳያ የስራ ክፍልዎ ያላከናወናቸው ጉዳዮች ካሉ ዋና ዋናዎቹን ቢገልፁልን፡- _______________________________________________________

   ____________________________________________________________________

   ____________________________________________________________________

   ____________________________________________________________________

13. የስራ ክፍልዎ ለደንበኞች የቴክኒክ እገዛ ግብረ መልስ ሰጥቶ ያውቃል?

   ሀ. አዎ ለ. የለም

14.የስራ ክፍልዎ ለደንበኞች ተገቢውን አገልግሎት ለመስጠት የቴክኒክ ብቃት ነበረው? (የቴክኒክ ብቃት ተፈላጊ አቅምን የቴክኒክ እገዛ ስታንዳርድ፣ መመሪያ፣ ወዘተ ያካትታል)

ሀ. አዎ ለ. የለም

15.ለ14ኛው ጥያቄ መልስዎ “አዎ” ከሆነ የስራ ክፍልዎ ተፈላጊውን የቴክኒክ በድጋፍ ለደንበኞች ለመስጠት የሚያስችል ብቃት ሲመዘን

ሀ. በጣም ከፍተኛ ለ. ከፍተኛ ሐ. መካከለኛ መ. ዝቅተኛ

16.ለ14ኛው ጥያቄ መልስዎ የለም ከሆነ ለምን? ______________________________

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

17.የስራ ክፍልዎ ለደንበኞች የቴክኒክ እገዛ በተገቢው ሁኔታ ለመስጠት እንዳይችል ያደረጉ ችግሮች ካሉ ቢዘረዝሩልን፡- ______________________________

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

18.በስራ ክፍልዎ የተሻለ አገልግሎት ለደንበኞች ለመስጠት መሻሻል የሚገባቸው ጉዳዮች ላይ አስተያየት ሲሰጡን፡-______________________________

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

19.የማጠቃለያ አስተያየት ካለዎት ቢሰጡን፡- ______________________________

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

**ይህን መጠይቅ ለመሙላት/ምላሽ ለመስጠት ላደረጉት ትብብር**

**የስራ ሂደት ጥናት ቡድኑ ከልብ ያመሰግናል፡፡**

# አባሪ 3፡ የስራ ክፍሎች አስተያየት ማጠቃለያ

1. መጠየቅ ከቀረበላቸው ዘጠኝ የሴክ/ጽ/ቤቱ የስራ ክፍሎች ዘጠኙም (100%) የቴክኒክ እገዛ ለማድረግ መነሻ እንደነበራቸው ምላሽ ሰጥተዋል፡፡
2. የሴክ/ጽ/ቤት የስራ ክፍሎች ለደንበኞች የቴክኒክ እገዛ ለመስጠት የሚያደርጓቸው ዋናዋና መነሻዎች፡-
   - ✓ በትብብር መድረኮች ላይ የሚነሱ አስተያየቶች
   - ✓ ለደንበኞች የሚቀርቡ የአካል፣ የደብዳቤና የስልክ ጥያቄዎች ፍላጎት
   - ✓ በመስክ ክትትል የታዩ የአሰራር ክፍተቶች
   - ✓ በወርክሾፖና ሪቪው ስብሰባዎች የሚነሱ ሃሳቦች
   - ✓ ከሪፖርቶች
   - ✓ ለድጋፍ የሚቀርቡ ፕሮጀክት ፕሮፖዛሎች፣
   - ✓ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጅዎች፣ ማንዋሎችና የአፈፃፀም መመሪያዎች
   - ✓ የረጂ ድርጅቶች የቴክኒክ እገዛ መስጠት ፍላጎት
   - ✓ የደንበኞች የመፈፀም አቅም
   - ✓ የሚሰጠው የቴክኒክ እገዛ አስፈላጊነት
   - ✓ የስራ ክፍሎች የቴክኒክ እገዛ የመስጠት አቅም
   - ✓ የመድረኮች ተመቻችቶ መገኘት
   - ✓ የአዳዲስ ፕሮግራሞችና አሰራሮች መምጣት
3. ለመጠይቅ ምላሽ የሰጡት ዘጠኝ የሴክ/ጽ/ቤት የስራ ክፍሎች በሙሉ (100%) ከጨ የቴክኒክ እገዛ ጥያቄ ተቀብለው የሚያውቁ መሆኑን ምላሽ ሰጥተዋል፡፡
4. ለመጠይቅ ምላሽ የሰጡት ዘጠኝ የሴክሬ/ጽ/ቤት የስራ ክፍሎች በሙሉ (100%) የደንበኞችን የአቅም ክፍተት ዳሰሳ ተሰርቶ አያውቅም ብለዋል፡፡
5. ለመጠይቅ ምላሽ ከሰጡት ዘጠኝ የሴክ/ጽ/ቤት የስራ ክፍሎች
   - 5 (55.6%) ያህሉ በዕቅድ ይንቀሳቀሱ ነበር፡፡
   - 4 (44.4%) ያህሉ ያለዕቅድ ይንቀሰሳቀሱ ነበር፡፡
6. ለደንበኞች ይሰጡ የነበሩ ዋና ዋናዎቹ የቴክኒክ እገዛዎች፡-
   - ✓ በአጋርነት መድረኮች ፈፃሚዎችን ማደራጀት
   - ✓ የአጋርነት መድረኮችን ጉባኤዎችንና ስብሰባዎችን ማመቻቸት

- ✓ ፈፃሚዎች የዕቅድ ማብራሪያ መስጠት፣ ማሳቀድ፣ የዕቅድ ማሻሻያ ሀሳብ መስጠት፣ ዕቅዳቸውን ማጠቃለል ሪፖርት መቀበል
- ✓ የፕሮጀክት ፕሮፖዛሎች እንዲስተካከሉ የቴክኒክ እገዛ ማድረግ
- ✓ ግንዛቤ ማስጨበጥ፣ ማንዋል ማሰራጨት፣ የዕቅድና ሪፖርት ቅጻቅጾች ማቅረብ
- ✓ የምክክር መድረኮችን ማዘጋጀት
- ✓ በደብዳቤና በአካል በመገኘት የአሰራር አቅጣጫ መስጠት
- ✓ የመስክ ጉብኝት በማድረግ የታዩ ችግሮችን ወዲያውኑ የመፍትሔ አቅጣጫ መስጠት /ግብረ መልስ መስጠት/
- ✓ ለስልጠናዎች የአፈፃፀም መመሪያ ማዘጋጀት የስልጠና ማቴሪያል ዝግጅትና ስልጠና መስጠት
- ✓

7. ለመጠይቅ ምላሽ ከሰጡት ዘጠኙም (100%) የስራ ክፍሎች መስጠት የነበረባቸው ነገር ግን ያልተሰጡ የቴክኒክ እገዛ ተግባራት ነበሩ ብለዋል፡፡
8. ለመጠይቅ ምላሽ ከሰጡት የሴክ/ጽ/ቤት የስራ ክፍሎች፡-

   በጥናትና ምርምር አኳያ ሌሎች አካላት ያጠኗቸውን በመደገፍ፡-

   - 4 (44.4%) ያከናወኗቸው ተግባራት አሉ፡፡
   - 5 (55.6%) ያከናወኗቸው ተግባራት የሉም፡፡
9. ከደንበኞች ፍላጐት አኳያ ያልተከናወኑ የቴክኒክ ድጋፍ ተግባራት፡-
   - ✓ ለደንበኞች ደረጃውን የጠበቀ የቴክኒክ ድጋፍ ያለመስጠት
   - ✓ መረጃ በወቅቱ ማቅረብ ያለመቻል
   - ✓ የፕሮፖዛል አዘገጃጀት
   - ✓ የዕቅድ አዘገጃጀት
   - ✓ ደንበኞች ጥሪ ሲያቀርቡ በአካል ተገኝቶ የቴክኒክ እገዛ ማድረግ
   - ✓ የትብብር መድረኮችን በመደበኛነት ያለማካሄድ
   - ✓ በአፈፃፀም የታዩ ችግሮችን በጥናት መፍትሔ ያለመስጠት
10. ለመጠይቅ ምላሽ ከሰጡት የሴክ/ጽ/ቤት የስራ ክፍሎች
    - 7 (77.8%) የቴክኒክ ድጋፍ ግብረ መልስ ሰጥተዋል፡፡
    - 2 (32.2%) የቴክኒክ ድጋፍ ግብረ መልስ አልሰጡም፡፡

11.ለመጠይቅ ምላሽ ከሠጡት የሴክ/ጽ/ቤት የስራ ክፍሎች የቴክኒክ እገዛ ለመስጠት ብቃታቸው ሲመዘን

- 3 (33.3%) ከፍተኛ
- 5 (55.5%) መካከለኛ
- 1 (11.1%) ዝቅተኛ

12. በቴክኒክ እገዛ አሰጣጥ የነበሩ ችግሮች፡-

- ✓ የሚያሰራ ወጥነት ያለው ስርዓት ያለመኖር
- ✓ የሠው ሃይል ተፈላጊ ብዛት ብቃት /የአቅም ውስንነት
- ✓ የደንበኞች ፍላጎት ከአቅም ጋር ያለመመጠን
- ✓ የመመሪያዎች በበቂ ያለመኖር
- ✓ የስራ መደራረብ /ወቅታዊ ስራዎች መደራረብ
- ✓ የደንበኞች አቅም ውስንነት

13.የተሻለ የቴክኒክ እገዛ ለመስጠት መሻሻል የሚገባቸው ጉዳዮች፡-

- ✓ የሰው ሃይል በብቃት ማጠናከር
- ✓ የቴክኒክ እገዛ ዝርዝር መመሪያ ማዘጋጀት (ደረጃውን የጠበቀ የቴክኒክ ድጋፍ አሰጣጥ መመሪያ)
- ✓ ደራሽና ተደራራቢ ስራዎችን መቀነስ
- ✓ ለቴክኒክ እገዛ አስፈላጊ ግብዓቶች አቅርቦት ማሻሻል
- ✓ ከደንበኞች ጋር የበለጠ ተቀራርቦ መስራት
- ✓ ከክልል እስከ ቀበሌ የሚደርስ የቴክኒክ እገዛ ስርዓት መዘርጋት
- ✓ ተጠያቂነት ያለው ሰርዓት በየደረጃው መዘርጋት
- ✓ ኘሮግራሞችን ከክልል እስከ ቀበሌ ማድረስ
- ✓ ለኘሮጀክት ምላሽ በመስጠት ረገድ የተንዛዛ አሰራሮችን ማስወገድ

# አባሪ 4፡ የፈጻሚ ደንበኞች አስተያየት ማጠቃለያ

## በቴክኒክ እገዛና ጥናት ዋና የስራ ሂደት ከፈጻሚዎች በመጠይቅ

## የተሰበሰበው መረጃ ማጠቃለያ

ለቴክኒክ እገዛና ጥናት ዋና የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት ለፈጻሚ አካላት ሊሰጡ የሚገባቸው የቴክኒክ ድጋፍ ፈላጎቶችን ለማወቅ በማሰብ የተለያዩ ጥያቄዎች ለ37 ፈጻሚ አካላት ቀርበው ከ31 ድርጅቶች ምላሽ ተሠጥቶባቸዋል፡፡ ለጥያቆች የተሰጡ ምላሾች ማጠቃላያ ከዘህ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

1. በኤች አይ ቪ/ኤድስ አስተቃቀድ ስልጠና ወይም የቴክኒክ እገዛ ስለማግኘታቸውና ያገኙትም ስለስልጠናው በቂነት ተጠይቀው 31 ፈጻሚ አካላት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ከነዚህም፤
   - 28 (90%) የስልጠናና የቴክኒክ እገዛ አግኝተዋል
   - 3 (10%) የስልጠናና የቴክኒክ አገዛ አላገኙም
   - 13 (41.9%) የተደረገው ድጋፍ በቂ እንደነበር ተቁመዋል
   - 12 (38.7%) የተደረገላቸው ድጋፍ በቂ እንዳልነበረ ምላሽ ሰጥተዋል
   - 4 (13%) እገዛ ያላገኙና ድጋፉን የሚፈልጉ ናቸዉ

2. የኤች አይ ቪን ጉዳይ ከመደበኛ ስራ ጋር አዋህዶ ለመስራት የሚያስችል (የሜይንስትሪሚንግ) ክህሎት ስለማግኘታቸውና ያገኙትም ስለክህሎቱ በቂነት ተጠይቀው በተሠጠ ምላሽ
   - 26 (83.4%) ክህሎቱን አግኝተዋል
   - 4 (13%) ክህሎቱን አላገኙም
   - 10 (32.2%) የተሠጠው እገዛ በቂ ነበር
   - 16 (51.6%) የተሠጠው እገዛ በቂ አይደለም
   - 5 (16.1%) ድጋፉን ቢያገኙ ይፈልጉ እንደነበር ገልጸዋል፡፡

3. የኤድስ ፈንድ አመሠራረትና አተገባበር በተመለከተ ስለተደረገላቸው እገዛና በቂነቱ ተጠይቀው ከፈጻሚ አካላት የተሠጡ ምላሾች
   - 24 (77.4%) ድጋፍ ተደርጎላቸዋል
   - 4 (13%) ድጋፍ አልተደረገላቸውም
   - 12 (38.7%) የተደረገው ድጋፍ በቂ ነበር
   - 10 (32.2%) የተደረገው ድጋፍ በቂ አልነበረም
   - 7 (22.6%) እገዛው ያልተደረገላቸውና ድጋፍ የሚፈልጉ ነበሩ

4. በደንበኞች እጅ የኤድስ ፈንድ መመሪያ ስለመኖሩና ስለመመሪያውም ለመስራት ስላለው በቂነት ተጠይቀው
   - 22 (70.9%) መመሪያ አላቸው
   - 8 (58.8%) መመሪያ የላቸውም
   - 11 (35.5%) መመሪያውን ለመስራት በቂ ነው
   - 13 (41.9%) መመሪያውን ለመስራት በቂ አይደለም
   - 8 (25.8%) መመሪያውን በመስጠት ድጋፍ ያልተደገላቸውና በቀጣይ ድጋፍ የሚፈልጉ ናቸዉ

5. ድጋፍና እንክብካቤን በተመለከተ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል ዕውቀትና ክህሎት እንዲኖራቸው የተደረገውን እገዛና በቂነቱን በተመለከተ ለቀረበው ጥያቄ ከፈጻሚ አካላት እንደሚከተለዉ ምላሾች ተገኝተዋል ፡፡
   - 18 (28.1%) የሆነ እውቀትና ክህሎት ያገኙ
   - 10 (32.2%) በቂ የሆነ እውቀትና ክህሎት ያላገኙ
   - 7 (22.8%) እገዛው ብቂ ነበር
   - 8 (25.8%) እገዛው ብቂ አልነበረም
   - 9 (29.9%) እገዛ ያልተደረገላቸውና የድጋፍ ፍላጎት የሚሹ

6. ድጋፍና ክብካቤ መመሪያ ስለመኖሩና በቂነቱ ለቀረበው ጥያቄ የተሠጠ ምላሽ
    - 7 (22.6%) መመሪያ አላቸው
    - 22 (70.9%) መመሪያ የላቸውም
    - 1 (3.2%) የተዘጋጀው መመሪያ በቂ ነው
    - 18 (58.1%) የተዘጋጀው መመሪያ ሊሻሻል ይገባዋል
    - 18 58.1%) መመሪያ የሚያስፈልጋቸው

7. በአጋርነት ሊመሰረት የሚያስችል እውቀት/ክህሎት ስለማግኘታቸውና የገኙትም ክህሎት በቂነት ተጠይቀው
    - 18 (58.1%) እውቀት/ክህሎት ያላቸው
    - 11 (35.5%) እውቀት/ክህሎት የላቸውም
    - 4 (12.9%) በቂ እውቀትና ክህሎት ያላቸው
    - 13 (41.9%) በቂ እውቀትና ክህሎት የሌላቸው
    - 8 (25.8%) ምንም አይነት ድጋፍ ያልተደረገላቸው

8. በዕቅድ ተይዘው ለሚፈጸሙ ተግባር ተገቢ የሆነ ክትትል ለማድረግ የሚያስችል እውቀት/ክህሎት ስለማግኘታቸው ተጠይቀው ላይ የተሠጠ ምላሽ
    - 12 (38.7%) የክትትል ስራ እውቀት/ክህሎት እንዲያገኙ የተደረጉ
    - 16 (51.6%) የክትትል ስራ እውቀት/ክህሎት ድጋፍ ያልተደረገላቸው

9. በኤች አይ ቪ/ኤድስ መከ/መቆ መሠረታዊ ዕውቀት የሚያስጨብጡ እገዛ ስለማግኘታቸውና ያገኙትም ስለበቂነቱ ተጠይቀው የተሠጠ ምላሽ
    - 23 (74.2%) መሠረታዊ እውቀት የሚሠጥ ድጋፍ ተደርጓል
    - 4 (12.9%) መሠረታዊ እውቀት የሚሠጥ ድጋፍ አልተደረገም
    - 6 (19.4%) በቂ እውቀት እንዲጨብጡ ድጋፍ የተሠጣቸው
    - 16 (51.6%) በቂ እውቀት የሚያስጨብጥ ድጋፍ አልተደረገም
    - 4 (12.9%) እገዛ ያለተደረገላቸውና እገዛውን የሚፈልጉ

10.የማህበረሰብ ውይይት ለማካሄድ የሚያስችል እውቀት/ክህሎት ስለማግኘታቸውና የገኙትም ስልጠና/ክህሎት በቂነት ተጠይቀው የተሠጡ ምላሾች

- 10 (32.3%) ክህሎት ያገኙ
- 21 (67.7%) ክህሎት አላገኙም
- 2 (6.5%) በቂ ክህሎት አግኝተናል
- 7 (22.6%) በቂ ክህሎት አልተሰጠንም
- 12 (38.7%) ድጋፍ ያልተደረገላቸውና እገዛ የሚፈልጉ

11.ሪፖርት አቀራረብ ሥልጠና ስለማግኘታቸውና ያገኙትም ስለስልጠናው በቂነት ተጠይቀው

- 7 (22.6%) ለሪፖርት ዝግጅት ስልጠና አግኝተዋል
- 18 (58.1%) ለሪፖርት ዝግጅት ስልጠና አላገኙም
- 3 (9.7%) የተሠጠን እገዛ በቂ ነበር
- 3 (9.7%) የተሠጠን እገዛ በቂ አልነበረም

12.ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከ/መቆ ስራዎችን መምራት የሚያስችል እውቀት/ክህሎት እንዲኖራቸው የሚያስችል እገዛ ስለማግኘታቸውና የገኙትም እገዛ በቂነት ተጠይቀው

- 7 (22.6%) ስልጠናውን አግኝተዋል
- 18 (58.1%) ስልጠናውን አላገኙም
- 3 (9.7%) የተሠጠው ስልጠና በቂ ነው
- 3 (9.7%) የተሠጠው ስልጠና በቂ አልነበረም

13.በአፈፃፀም ወቅት ያጋጠማቸውን ችግሮች ለመፍታት ከሴክሬታሪያት ጽ/ቤቱ የቴክኒክ እገዛ ስለመጠየቃቸውና ስለማግኘታቸው ስላገኙትም እገዛ በቂነት ተጠይቀው

- 22 (70.9%) እገዛውን ጠይቀዋል
- 7 (22.6%) እገዛውን አልጠየቁም
- 15 (48.4%) የተሠጣቸው የቴክኒክ እገዛ በቂ እንደነበር የገለጹ
- 5 (16.1%) የተሠጣቸው የቴክኒክ እገዛ በቂ አለመሆኑን የገለጹ

14.የሕዝብ ንቅናቄ ለማድረግ የተከናወኑ ስራዎች ያጋጠሙ ችግሮች በተመለከተ የተሠጡ ምላሾች

- 18 (58.1%) የአፈፃፀም ችግሮች ነበሩ
- 7 (22.6%) የአፈፃፀም ችግሮች አልነበሩም

15.በህዝብ ንቅናቄ አፈፃፀም ወቅት ለተፈጠሩ ችግሮች ከሴክሬታሪያቱ ጽ/ቤታችን የቴክኒክ እገዛ ፍላጐት ነበር

- 13 (41.9%) የቴክኒክ እገዛ ተጠይቀል
- 13 (41.9%) የቴክኒክ እገዛ አልተጠየቀም

16.ኤች አይ ቪ/ኤድሰ በመ/ቤትዎ ሠራተኞችና አገልግሎት በምትሠጡት ደንበኛ ላይ እያደረሰ ያለው ተፅዕኖ ስለመጠናቱና ለጥናቱም ስለተደረገው እገዛ በቂነት ተጠይቀው በምላሹ

- 4 (12.9%) ተጠንቷል
- 23 (74.2%) አልተጠናም
- 25 (90.6%) ጥናት ለማካሄድ የቴክኒክ ድጋፍ የሚፈልጉ
- 9 (29%) በኤች አይ ቪ/ኤድስ ዙሪያ የጥናት ሰነድ የደረሳቸው
- 19 (63.1%) በኤች አይ ቪ/ኤድስ የተካሄዱ ልዩልዩ የጥናቶች ሰነድ ያልደረሳቸው
- 7 (22.6%) የጥናት ሰነዶች የደረሳቸው መ/ቤቶች የጥናቶችን ግኝቶች ለስራቸው ደጋፊ እንደነበሩ አመልክተዋል

17. ከመ/ቤታቸው ሥራ ጋር ተቀራራቢነት ባለው ከኤች አይ ቪ/ኤድስ በተገናኘ መጠናት ያለባቸውን ጉዳዮች በተመለከተ

- 19 (63.1%) የሚጠኑ ጉዳዮች አሉ
- 9 (29.6%) የሚጠኑ ጉዳዮች የሉም

18. በስራና በመኖሪያ አካባቢዎቻቸውና በክልሉ ኤች አይ ቪ/ኤድስን የሚያስፋፉ ጉዳዮችን በተመለከተ

- 18 (58.1%) የሚያስፋፉ ጉዳዮች አሉ
- 4 (12.9%) የሚያስፋፉ ጉዳዮች የሉም

19.ያላገኙት ግን ደግሞ በኤች አይ ቪ/ኤድስ ዙሪያ የሚፈልጉበት የጥናት ውጤት ስለመኖሩ ተጠይቀው

- 20 (64.5%) የሚፈልጉት የጥናት ውጤት አለ
- 7 (22.6%) የማይፈልጉት የጥናት ውጤት የለም

በአባሪ አንድ በቀረበው መጠይቅ ከዚህ በታች ያለውን የጠያቄ ቁጥር ለያዙ ዝርዝር መግለጫ ለሚጠይቁ ጥያቄዎች ፈጻሚዎች የሰጡት ዝርዝር የጽሁፍ ምላሽ በሚከተለው መልኩ ተጠቃልሎ ቀርቧል።

1.14. ደንበኞች ከጽ/ቤታችን የሚፈልጉትን የቴክኒክ እገዛ በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ ሲመልሱ ዋና ትኩረታቸው ሥልጠና ማግኘት ሆኖ በአብዛኛው አቅም ግንባታ ጋር የተያያዘ ነው።

ከሥልጠና ፍላጎቶቻቸው መካከል የሜይንስትሪሚንግ፣ በኤድስ ፈንድ፣ የአመራር፣ በትብብር መድረክ በጋራ የመስራት፣ አቻ ለአቻ ውይይት፣ የክትትልና ግምገማ፣ የፕሮጀክት ቀረፃና መነሻ ሃሳብ፣ ስለበጎፈቃደኝነት፣ የሕዝብ ንቅናቄ ስለመፍጠር፣ የግንኙነት ክህሎት፣ የዕቅድ አዘገጃጀትና ሪፖርት፣ የሚሉት የስልጠና ርዕሶች በተደጋጋሚ ተጠቅሰዋል ሌሎች እገዛዎችን በተመለከተም የተለያዩ መመሪያዎችና ማኑዋሎች፣ መረጃዎች የአሠራር አቅጣጫዎች፣ የልምድ ልውውጦችና በጋራ አድቮኬሲ ለማካሄድ የሚያስችል ሁኔታ እንዲፈጠርላቸው እንደሚፈልጉ ገልፀዋል።

2.2 በሕዝብ ንቅናቄ ላቀረቡት የእገዛ ጥያቄ አውንታዊ ምላሽ ካገኙት የተሰበሰው አስተያየት ተገቢውን እገዛ እንዳገኙና በቂ እንደሆነ ገልፀው የተወሰኑ ደንበኞች ግን ባለሙያዎችን በጊዜና በተፈለገ ቦታ ማግኘት እንዳልተቻለ ገልፀዋል።

3.1. ኤች አይቪ/ኤድስ በመ/ቤታቸው ላይ እያደረሰ ያለውን ጥፋት ያላጠኑበትን ምክንያት ደንበኞች ሲገልፁ የኃላፊዎች የትኩረት ማነስ፣ የገንዘብ የሰው ኃይልና የሙያ እጥረት በተደጋጋሚ የቀረቡ ምክንያቶች ሲሆኑ ስለመጠናቱ ግንዛቤ እንደሌላቸውም የገለፁ አሉ።

3.2. ኤች አይ ቪ/ኤድስ በመ/ቤታቸው ላይ ያደረሰውን ጉዳት ጥናት ለማካሄድ ደንበኞች የሚፈልጉትን የቴክኒክ እገዛ ተጠይቀው፤ ስለተፅእኖ ትንታኔ (Impact Analysis) እና በኤችአይቪ/ኤድስ ዙሪያ ስለሚደረጉ ጥናቶች አካሄድ ስልጠና ቢያገኙ እንደሚፈልጉ ገልፀዋል።

3.4 ከሥራቸው እና ከኤች አይ ቪ/ኤድስ ጋር በተገናኘ መጠናት ያለበትን ጉዳይ አስመልክቶ ደንበኞች የሚከተሉትን ጠቁመዋል።

- የገቢ ማስገኛ አካሄድና ውጤት፣ ለምን በተደጋጋሚ ውጤታማ እንደማይሆን፣
- አሳዳጊ ያጡ ሕፃናት አኗኗርና የተሻለ ሁኔታ ስለመፍጠር፣
- የሥራ ቦታ ውይይት እንዴትና በምን ሁኔታ ማካሄድ እንደሚቻል፣
- ኤች አይ ቪ በደማቸው ያለ ወገኖችና ሕግ፣ ኤች አይ ቪ በደማቸው ያለ ወገኖች ኤች አይ ቪን በመከላከል ያላቸው ሚናና ድጋፍ፣
- ኤች አይ ቪና ተፅእኖው በትምህርት ላይና በትምህርት ውስጥ
- የማሕበረሰብ ንቅናቄ ስለመፍጠር በተመለከተ ማጥናት እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል፡፡

3.5ለ- ለኤች አይ ቪ/ኤድስ መስፋፋት አስትዋጽኦ የሚያደርጉ ደንቦችና ልምዶችን በተመለከተ

- ኮንዶም መጠቀም ላይ በሕዝቡም ይሁን በእምነት ሰዎች ያለው አመለካከት ፣
- የት/ቤቶች አርፋጅ ተማሪዎች አቀጣጥ (ግቢ አለማስገባት)፣
- ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች (ያለዕድሜ/ያለአቻ ጋብቻ፣ውርስ ጋብቻ፣ ዋርሳ፣ ቅምጥ፣ ፍቺ፣ ንቅሳት፣ የሴት ልጅ ግርዛት፣ እንጥል መቁረጥ፣ ግግ ማስፈልፈል፣ ሴተኛ አዳሪነት፣ የፆታ ጥቃት)፣
- የቪዲዮ፣ ጫት ቤትና ጭፈራቤቶችና ደባል ሱሶች ተጠቅሰዋል፡፡

ሐ- እነዚህን ችግሮች ለማቃለል መውሰድ ያለበትን እርምጃ በተመለከተም

- ፈፃሚዎችን በአቅም ማጠናከርና የሕዝብ ንቅናቄ መፍጠር፣
- ተከታታይ ትምህርቶችና ስልጠናዎች ውይይቶች ማካሄድ፣
- ልማዳዊ ጎጂ ድርጊት ፈፃሚዎችን ማሳተፍና አመለካከታቸውን መቀየር፣
- ከሕግ አካላት ጋር በጋራ መስራትና ለሕግ አውጪዎች መስተካከል ያለበትን በጥናት አሳደግፎ ማቅረብ ተጠቁሟል፡፡

3.6ለ - ደንበኞች የሚፈለጉት ግን ያለገኙት የጥናት ውጤቶች ካሉ ተጠይቀው ጥቂቶቹ የተወሰኑ ጥናቶችን ጠይቀዋል፡፡ አማራ ክልል ለምን በኤችአይቪ የበለጠ ተጠቃ፣ ኤች አይ ቪ በደማቸው ያሉ ሰዎች የመከላከል ሚና ማኑዋልና መመሪያዎችንም የጠየቁ አሉ፡፡ ሆኖም በዋናነት ያሉትን ጥናቶች ያለማወቅና አሉ የሚባሉትን የማግኘት ፍላጎት በስፋት ተንፀባርቋል፡፡

3.7 በኤች አይ ቪ/ኤድስ ዙሪያ ሊጠኑ የሚገባቸውንና የተካሄዱ ጥናቶች በተመለከተም ሲመልሱ፡

- ያሉትን ጥናቶች ማስተዋወቅና ማሠራጨት
- በየመ/ቤቱ ኤችአይቪን የመከ/መቆ/ ሥራዎችን ለመተግበር አንድ ሠራተኛ ሊኖረው የሚችልበት አግባብ ቢኖር
- የችግሩ ተጋላጮች ሁኔታና ፍላጎት ቢጠና
- የሚመጡ አዳዲስ ሠራዎች በጥናት ላይ የተመሠረቱ ቢሆኑ
- የእስካሁኑ ጥረታችን ያመጣው ውጤት ቢጠና
- የገቢ ማስገኛዎች ዝቅተኛ ውጤታማነት ምክንያቶች
- ለመሸታው የበለጠ ተጋላጭ የሚሆኑ የሕብረተሰብ ክፍሎች እና ኤች አይ ቪ በደማቸው ያለ ሴቶችና ሕፃናት ጉዳይ ቢጠና
- ወደፊት የበለጠ ውጤት ለማምጣት በምን ላይ እናተኩር የሚሉት ቢጠኑ የሚለ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

3.8 ጽ/ቤታችን ወደፊት ሊያተኩርባቸው የሚገባ ጉዳዮችን በተመለከተ፤

- በተለይ ለአዳደስ የኤች አይ ቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ሥራ ተጠሪዎች ለነባሮችም በቂ ስልጠናና የመሥራያ መመሪያዎች መስጠት
- የኤች አይ ቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ሥራ ባለቤትና ተጠያቂነት ባለው መልኩ በሁሉም መ/ቤቶች እንዲኖርና በቅንጅት መሥራት እንዲችሉ ማድረግ
- ተከታታይ ክትትልና ግምገማ
- ኤች አይ ቪ በደማቸው ያለባቸው ወገኖች ማሕበራትን ማገዝ
- የሥራ ቦታ ንቅናቄ መፍጠር
- የተሻሉ ተሞክሮዎችን ማሰባሰብና በተከታታይ ማሳተም
- የትብብር መድረኮችን (GO- NGO ትብብርን ጨምሮ) ማደራጀትናና ማጠናከር
- ከገንዘብ መስጠቱ ባልተናነሰ በስፋት የሙያ እገዛ በመስጠት አቅም ማሳደጉ ላይ ቢያተኩር
- በተለይ ገቢ ማስገኛ፣ ከእናት ወደ ልጅ፣ የሕፃናት ፀረ ኤች አይ ቪ፣ ልዩ ትኩረት የሚሹ ቦታዎች ላይ የተጠናከረ ሥራ ቢሠራ
- ውጤታማነታቸው በጥናት የተረጋገጠ ኢንተርቬንሽኖችን ብቻ ሥራ ላይ እንዲውሉ ቢያደርግ የሚሉት አስተያየቶች በስፋት ተነስተዋል፡፡

## አባሪ5፤የነባሩ አሰራር ለሚከናወኑ ተግባራት የሚያስፈልገው ወጪ

| ተ.ቁ | ተግባራት | ደመወዝ | ውሎ አበልና ተዛማጅ ወጪዎች | መስተንግዶና ተዛማጅ ወጪወች | የፅህፈት መሳሪናየና ተዛማጅ ወጪዎች | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1) | የቴክኒክ እገዛ ዕቅድ ማዘጋጀት | 7ሰውX4500(70%) X12= 88,200 | | | 4,000 (በሩብዓመት1000) | 92200 |
| 2) | የቴክኒክ እገዛ መስጠት | 7ሰውX4500(20%) X12= 3,600 | 55,440 | | 4,000 (በሩብዓመት1000) | 63040 |
| 3) | የቴክኒክ እገዛ ሪፖርት ማዘጋጀት | 7ሰውX4500(10%) X12= 1,800 | | | 4,000 (በሩብዓመት1000) | 5800 |
| 4) | ስትራቴጅዎችንና ዝርዝር የአፈፃፀም ኘሮግራሞችን ክልላዊ ይዘት መስጠት | 7ሰውX4500(60%) = 18,900 | | | 4,000 (በሩብዓመት1000) | 22900 |
| 5) | ስትራቶጅወተንና ዝርዘር የአፈፃፀም ኘሮግራሞተን ማስተዋወቅ | 7ሰውX4500(30%) = 9,450 | 252,000 | 28,000 | 2,000 | 291450 |
| 6) | ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያዎችን ማስተላለፍ | 7ሰውX4500(10%) = 3,150 | | | 12,000 (3000 በሩብ ዓመት) | 15150 |
| 7) | አድቮኬሲ ማካሄድ | 7ሰውX4500(30%) X2= 18,950 | 504,000 (2 ጊዜ በዓመት) | 56,000 | 4,000 | 582900 |
| | ድምር | 144,000 | 811,440 | 84,000 | 34,000 | 1,073,440 |

## ማውጫ


1. መግቢያ ........ 1

1.1. የስራ ሂደቱ ቅኝት ........ 1
1.2. የጥናቱ ዓላማ ........ 2
1.3. የጥናቱ ግብ ........ 2
1.4. የጥናቱ አስፈላጊነት፡- ........ 2
1.5. የጥናቱ ወሰን /Scope/ ........ 2
1.6. የጥናቱ ዘዴ ........ 2

2. ነባሩን የስራ ሂደት መተንተን ........ 3

2.1. ነበሩ የስራ ሂደት የት ጀምሮ የት ያበቃል? ........ 3
2.2. የስራ ሂደቱ ግብዓት፣ ውጤትና የግብ ስኬት ........ 3
2.3 የቴክኒክ እገዛና ጥናት ዋና የስራ ሂደት ፍሰት (High Level Map) ........ 4
2.4. የነባሩ የስራ ሂደት ዝርዝር ፍሰት (Detail Map) ........ 5

3. ነባሩን የስራ ሂደት ማጥናት ........ 8

3.1. የስራ ሂደቱ ምን ውጤት ያስገኛል? ........ 8
3.2. የስራ ሂደቱ ይህን ውጤት ለምን አስገኘ? ........ 8
3.3. የስራ ሂደቱ ደንበኞችና ፍላጎት ........ 8
3.4. ሌሎች ባለድርሻዎችና ፍላጎቶቻቸው ........ 8
3.5 የነባሩ የስራ ሂደት የአፈጻጸም ደረጃ (Performance Baseline) ........ 9
3.6. የስራ ሂደቱ ችግሮች፣ ህጎችና ታሳቢዎች (Problems, Rules & Assumptions) ........ 10

አባሪ 1፤ የፈፃሚዎች አስተያየት ማሰባሰቢያ መጠይቅ ........ 12

አባሪ 2፡ የጽ/ቤቱ የስራ ክፍሎች አስተያየት ማሰባሰብ መጠይቅ ........ 17

አባሪ 3፡ የስራ ክፍሎች አስተያየት ማጠቃለያ ........ 20

አባሪ 4፡ የፈጻሚ ደንበኞች አስተያየት ማጠቃለያ ........ 23

አባሪ5፤የነባሩ አሰራር ለሚከናወኑ ተግባራት የሚያስፈልገው ወጪ ........ 31

# የቴክኒክ እገዛና ጥናት ዋና የስራ ሂደት

# አሁን ያለው ሁኔታ

# (AS-IS)

የአብክመ ኤችአይቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ሴክሬታሪያት ጽ/ቤት

ጥቅምት12 ቀን 2001 ዓ.ም.

ባሕርዳር